# የሚታዘነውስ ለነ አቶ መለስ ዜናዊ ነዉ !

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

መጋቢት 20 ቀን 2002

የእህታችን የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የጤና ሁኔታ ብዙዎቻችንን እያሳሰበና እያስጨነቀ እንደሆነ አስባለሁ። ሊያስጨንቀንና ሊያሳስበንም በርግጥ ይገባል። የርሷ ሕመም የእያንዳንዳችን ሕመም ነዉ። በርሷ ላይ የሚደርሰዉ በኛ እንደደረሰ ነው። እርሷ ስታቃስት እኛም እናቃስታለን። ከዚህ በፊት በአንድ ጽሁፌ እንደገለጽኩት፣ እኛም አላማዋን አላማችን አድርገን ይዘን የተነሳን «ብርቱካን ሚደቅሳዎች» ነን። አራት ኪሎ ያሉ ባለሥልጣናት አንዷቷን ብርቱካን ሚደቅሳ በአካል ቢያስሯትም በአሥር ሚሊዮን የሚቆጠሩ ብርቱካን ሚደቅሳዎች ተወልደዋል።

በተለይም በዚህ የጌታችንና የመድሃኒታችን የየሱስ ክርስቶስ ሕማምን በምናስብበት ሳምንት፣ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የደረሰዉን ስቃይ ሳስብ፣ በሥጋ ዉስጤ ቢቆጣና ቢያዝንም፣ በመንፈሴ ግን ተጽናናዉ። ከሁሉም በላይ የሆነ፣ የተረሱትን የሚያስታወስ፣ የወደቁትን የሚያነሳ፣ ለተበደሉት የሚፈርድ፣ ለድሃ አደጎች የሚራራ፣ ትእቢተኞችን የሚያዋርድ  አምላክ እግዚአብሄር በሰማይ እንዳለ ሳስብ ልቤ በደስታ ተሞላ።

ከሁለት ሺህ አመታት በፊት፣ አንድ አርብ ቀን፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባላጠፋዉ ጥፋት፣ የሰዉ ልጆችን በሙሉ ከሐጢያት ለማዳን እንደ ወንበዴ ተቆጠረ። ይከተሉት የነበሩ ደቀ መዛሙርት ሁሉ ሸሹ። ትላንት በሽተኞች ሲፈዉሱና ድንቅ ተዓምራት ሲያደርግ በሺሆች እንዳልተከተሉት ሁሉ፣ የዚያን አርብ ቀን ግን፣ ከጎኑ የሚቆም ጠፋ። ተጠማሁ ባለ ጊዜ ሆምጣጤ አጠጡት። የሾህ አክሊል በራሱ ላይ ጫኑበት። ገረፉት። በሚስማር እጆቹንና እግሮቹን ወግተዉ ሰቀሉት። «ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሳባክታኒ- አምላኬ አምላኬ ለምን ተዉከኝ» ብሎ ጮኸ። ነፍሱን አሳልፎም ሰጠ። ፀሐይ ብርሃኗን መስጠት አቆመች። መሬት ተንቀጠቀጠች። የደመናዉ ጥቁረት ያስፈራና ያስደነግጥ ነበር። አዎ የያኔዋ አርብ ቀን የሐዘንና የልቅሶ ቀን ነበረች።

ከሶስት ቀናት በኋላ መቃብር ፈንቅሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሳ። « ክርስቶስ ትንሳዔ ሙታን፣ ሞተ ይኬዶ ለሞት፣  ለእለ ዉስጥ መቃብር፣  ወካቤ ሕይወት ዘለአላም እረፍት» እንደተባለዉ ክርስቶስ ሞትን ድል ነሳ። ከሰማይ ብርሃን ተገለጠ። ደስታና ዝማሬ ሆነ።

ይህ የጌታ የትንሳዔ ዜና የሚያስተምረን አንድ ትልቅ ቁም ነገር ቢኖር፣ እንደጨለመ እንደማይቀር ነዉ። ዛሬ ዓርብ በመሆኑ ጉልበተኞች፣ ከፉዎችና  ጨካኞች ደም እያፈሰሱ ይሆናል። ዛሬ ዓርብ በመሆኑ ወንጀል ያልሰሩ፣ መልካም ያደረጉ፣ ፍቅርን ያስተማሩ

ታስረዋል። ዛሬ ዓርብ በመሆኑ እነ ብርቱካን ሚደቅሳ በማንም ነፈሰ ገዳይ ላይ ያልደረሰ ግፍ እየደረሰባቸዉ ነዉ። ዛሬ ዓርብ በመሆኑ ፍርድ እየተዛባ ነዉ። ዛሬ በነ አቶ መለስና በነካድሬ ሽመልስ ከማል ዉስጥ ያለ የጭካኔ፣ የዉሸት፣ ሰይጣናዊ መንፈስ ያየለ የሚመስልበት ጊዜ ነው። ዛሬ ብዙዎቻችን እያለቅስን ያለንበት ጊዜ ነዉ።

ነገር ግን እንደ ጨለመ አይቀርም። እንዳለቀስን አንቀርም። እሁድ ይመጣል። ዛሬ ያስጨነቁን የሚጨነቁበት፣ ዛሬ ያስለቀሱን የሚያለቅሱበት ጊዜ ይመጣል። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ትፈወሳለች። ከሕጻን ልጇና ከአሮጊት እናቷ ጋር እንደገና በቤቷ ማእድ ትቀርባለች። እንደገናም ድምጿን እንሰማለን። የፍቅር፣ የሰላም የይቅርታ የወንድማማችነት መልእክቶቿም ይደርሱናል። እንደ ደራርቱ ቱሉ የኢትዮጵያ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ በላይዋ ደርባ በአካልና በጤና እናያታለን።ይህንን ደግሞ የሚያደርገዉ ሁሉን እየተመለከተ ያለዉ የሰማይ አምላክ እግዚአብሄር ነዉ። (እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገዉ ደግሞ እግዚአብሄር የሚሰራዉ በሰዎች እንደሆነ ነው። እኛ ከዝምታ ወጥተን እግዚአብሄር ለሚወደዉ ፍትህ ለመቆም ስንነሳ ያኔ እግዚአብሄር በኛ ዉስጥ ይሰራል)

ይህን ብዬ አንድ ነጥብ ላንሳ። ሁኔታዉን በተለየ ማእዘን ካየነዉ ሊታዘን የሚገባዉ ማስተዋል አጥተዉ ግፍ እየፈጸሙ ላሉ ሰዎች እንደሆነ አስባለሁ። አላወቁትም እንጂ እነ አቶ መለስ እየተዋረዱና እየቀለሉ መምጣታቸዉ በገሃድ እየታየ ነዉ። ምናልባት ከዉጭ አገር መንግስታት በተገኘ እርዳታ መንገዶችና ግድቦች በመሰራታቸዉ ታሪክ በጥሩ ሊያስታውሰን ይችላል የሚል እንጭጭ አስተሳሰብ ሊኖራቸዉ ይችል ይሆናል። አይደለም። ከታሪክ መማር ይቻላል። የግራዚያኒን አገዛዝ ኢትዮጵያዉያን የምናስታዉሰዉ በተሰሩ መንገዶችና ድልድይች አይደለም። የካቲት 12 ቀን በጨረሳቸዉ ከሶስት መቶ ሺህ በላይ ኢትዮጵያዉያን እንጂ። መንግስቱ ኃይለማሪያምን የምናስታወሰዉ በሰራዉ የባሮ ድልድይ አይደለም። ነገር ግን በረሸናቸዉና ባስረሸናቸዉ በሺህ የሚቆጠሩ ንጹሃን ዜጎች እንጂ።

አቶ መለስ ደከምኩበት፣ ለፋሁበት የሚሉት ቢኖርም በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ አሁንም የቀጠለዉ ጭካኔያቸዉ፣ ሁሉ ነገር እንዲሸፈን አድርጎታል። የነበረችዉ ሌጋሲይቸዉ አንድም ትሁን ሁለት፣ ዜሮ ገብታለች። ከስረዋል፣ ተዋርደዋል። ወድቀዋል። ኮትና ክራባት አድርገዉ በቴሌቭዥን ሲታዩ ሰዉ ሊመስሉ ይችላሉ፤ ነገር ግን በሕዝብ የተናቁና የተጠሉ፣ ከሕዝብ ሸሽተዉ በፍርሃት ተደብቀዉ የሚኖሩ ሰዉ ሆነዋል። እንደ አገር መሪ ሳይሆን እንደ ነፈሰ ገዳይ እንደ ጨካኝ፣ እንደ ክፉ፣ እንደ ቂመኛ ነዉ እየታዩ ያሉት። ከዚህ የበለጠ ታዲያ ዉርደት፣ ከዚህ የበለጠ የሚያሳዝን ነገር ምን አለ ? የሚያሳዝነዉ ደግሞ አቶ መለስ ይሄን ሁሉ በራሳቸዉ ላይ ያመጡት እራሳቸዉ ናቸዉ።

በቅርቡ የነ አቶ መለስ ዜናዊ ቃል ቀባይ የሆኑት አቶ ሽመለስ ከማል የተባሉ፣ የሕግ ትምህርት ተምሪያለሁ የሚሉ ሰዉ፣ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታመም ላይ የሰጡትን አስተያየት ሪፖርተር ላይ አነበብኩኝ። ወ/ት ብርቱካን እንደማንኛውም እስረኛ በማረሚያ

ቤቱ ልታገኘዉ የሚገባ ማንኛውንም ጥቅሞች የማግኘት መብት እንዳላት፣ ነገር ግን ከሌሎች እስረኞች የተለየ ልዩ መብት ሊሰጣት እንደማይችል ነበር የገለጹት።

ሌሎች እስረኞችን ሊጠይቁ የመጡ ሁሉ ለአንድ ሰዓት ያህል፣ ከሰዓት በኋላ ያለ ገደብ መጠየቅ ይፈቀድላቸዋል። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ግን ጠዋት ለሰላሳ ደቂቃ በእናቷና በሕጻን ልጇ ከመጎብኘት በቀር ማንም ሌላ ሰዉ እንዲጎበኛት ሕግ ወጥ በሆነ መንገድ የተከለከለች እሥረኛ ናት። የቱ ላይ ነዉ ታዲያ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንደሌሎች እሥረኞች የታየችበት ሁኔታ ?

ሌሎች እስረኞች፣ ሴቶችን በጉልበት የደፈሩና ነፍስ ያጠፉ ሁሉ ሳይቀር፣ በእሥር ቤት ዉስጥ ሙሉ መብታቸዉ ሲጠበቅ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ግን ለስድስት ወራት በጨለማ ቤት ዉስጥ ተቀምጣ የስነ ልቦና ቶርቸር ሲደረግባት ቆይቷል። የቱ ላይ ነዉ ታዲያ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንደ ሌሎች እስረኞች የታየችበት ሁኔታ ?

እንደ አቶ ሽመለስ ከማል አይነቶቹ እዉነትን እያወቁ የከፋትና የዉሸት ተምሳሌት ሆነው በአደባባይ አፋቸዉን ሲከፍቱ መስማት፣ እንደ ሰዉ፣ እንደ ኢትዮጵያዊ የሚያሳፍር ነዉ። አቶ ሽመልስ በርግጥ ለራሳቸዉ ስብእና ክብር የሌላቸዉ እንስሳ መሆናቸዉን ነዉ በሚናገሩት ነገር በገሃድ እያሳዩን ያሉት። እንዲህ አይነቱ ሰዎች አላወቁትም እንጂ ፈረንጆች ሳይኮፓት የሚሏቸዉ በሽተኞች ናቸዉ። እግዚአብሄር ያስባቸው !

ለሁላችንም ቸር ይግጠመን !
እህታችንንም ቸሩ መድሃኔ አለም ባለችበት ቦታ ያበርታት!